# ኪ ዳ ና ች ን

# KIDANACH'N


ልዩ ዕትም መስከረም ፩ ቀን፥ ፳፻፱ (፪ሺ፱) ዓመተ ምሕረት

**Special Edition** **Meskerem 1, 2009 A.D (September 11, 2016)**


**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፥**
**ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኾናቸውን ለማስረዳትና**
**የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያ ልጆች የኾነውንም ኹሉ፡ ለመጠበቅ፥ ለማሳወቅም፡**
**በ"ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት" እየተዘጋጀ የሚወጣ ዕትም።**

**Published by "Ethiopia: The Kingdom of God"**
**to reveal the Divine Truth about Ethiopia's entity as the Kingdom of God**
**and Ethiopians' identity as the People of the Holy Covenant with God;**
**and so, to safeguard and promote all that pertains to Ethiopia and Ethiopians.**

# የ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ ምሕረት፡
# ቀን መቍጠሪያ

## 2009 (2016-2017 Gregorian) Calendar


**አዘጋጅ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ።**

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ
ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ-ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ
ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ

The Triumphant Lion of the Tribe of Judah
God The Son Jesus Christ
Eternal Priest in the Order of Melcke-Zedeq the Ethiopian
King of Zion and King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
እግዚአብሔር እም፡ድንግል ማርያም
እሙ ለመሲሕነ፥ ወእምነ ዘዚአነ
ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ

Ethiopia stretches out Her Hands to God
God The Mother The Virgin Mary
Mother of Our Messiah and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia

# ልዑል እግዚአብሔር፡

ከዘመነ ዮሓንስ፡ ወደዘመነ ማቴዎስ አሸጋግሮ፡
የኢትዮጵያን የነጻነት ህልውና በዓላችንን፡ ፯ሺ፭፻፱ኛ ዓመት፥
እና
የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያምን፡ ፪ሺ፳፭ኛ ዓመት፥
የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕን፡ ፪ሺ፱ኛ ዓመት፡
የትስብእት ልደታት በዓሎቻችንን፡ ለማክበር ለበቃንበት፡
ለአዲሱ፡ የ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ ምሕረት፡
እንኳን አደረሰን!

\+ + +

# <u>ስለቀን መቁጠሪያው መግለጫ።</u>

*፩ኛ፦ ይህ የቀን መቍጠሪያ የተዘጋጀው፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለውበ<u>፲፱፻፺፫</u> ዓ. ም. በታተመው መጽሓፍ ውስጥ የተገለጹትንና አግባብነት ያላቸውን ሓተታዎች መሠረት በማድረግ ነው።*

*፪ኛ፦ "በዘንዜከር" በተባለው፡ የየዕለቱ የጸሎት መግቢያ፡ ለመዓልቱና ለሌሊቱ ቅመራ፡ መነሻ ኾኖ፡ ከሌሎቹ ቍጥሮች ጋር የሚደመረው የ፳፻፱ቱ (የዕሥራ ምእት ተስዓቱ) [የ፪ሺ፱ኙ] ዓመተ ምሕረት፡ ዓበቅቴው፡ ፫ [ሦስት]፥ መጥቅዑ፡ ፳፯ [ሃያ ሰባት] መኾኑ ይታወቅ።*

*፫ኛ፦ በቀን መቍጠሪያው ሠንጠረዥ ውስጥ፡ በስም ብቻ የተጠቀሱት ቅዱሳንና ቅዱሳት ነቢያትና ሐዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት፡ ሌላ መግለጫ ካልተሰጠ በቀር፡ ዕረፍታቸውን፥ የአኀዞቹ [የቍጥሮቹ] የተለያዩ ቀለማት ደግሞ፡ ከዚህ የሚከተሉትን አብነቶች ያመለክታሉ፦*

*ሀ. ቀዩ፡ በእሑድ የቀጠለችውን ሰንበትን፥ ዐበይት በዓላትንና ተከታታዮቹን የፍስክ ዕለታትና ሳምንታት፤*

*በ. አረንጓዴው፡ ንኡሳን በዓላትን፤*

*ገ. ሰማያዊው፡ የአጽዋማት ቀኖችንና ሳምንቶችን የሚያሳዩ ናቸው።*

*፬ኛ፦ መስከረም ፩ ቀን፦*

*-ምናልባት፡ በእየራሳችን ድክመትና ስሕተት፥ ጕድለትና ጥፋት፡ ያሳደፍነውና ያበላሸነው፥ ያሰነካከልነውና ያስረጀነው፡ አካላዊና ባሕርያዊ የኾነ፡ ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና አምልኮአዊ የምንዝርና ግብር ቢኖር፡ ያን ኹሉ፡ የርኵሰትና የልክስክስነት ግብስብስና ዝባዝንኬ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ፈጽመን፡ ከሰውነታችን በማስወገድ፡ ወዲያ አውጥተንና አሽቀንጥረን ጥለን፤ ኹለንተናችንን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች አንጽተን ያደስንባት፤*

*-ከዚህም ጋር፡ ለእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና ለልጇ ለወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የልደት በዓላት ክብር፡ ሥጋችንንና ነፍሳችንን፥ መንፈሳችንንም፡ ቅዱስ ቁርባናችን በኾነው፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን የምናበቃባት፤*

*-ሰላማችንን ያስገኘልን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ድኅነትን ካስገኘችልን፡ ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን የተጐናጸፍነውንና የተቀዳጀነውን፡ የዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል፡ እንደአዲስ ተጇሚና ተሸላሚ ባለድል የተቀበልንባት፤*

*-ከአሮጌው፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን ትንሿን ትርፍ የጳጉሜን ወር፡ በንስሓ፥ በጋድ ጾምነትና ንኡስ ሱባዔነት፡ የምስጋና ጾምና ጸሎት አድርገን ያሳለፍንላት መኾኗ ሊዘከር [ሊታሰብ] ይገባል።*

*፭ኛ፦ በቀን መቍጠሪያው፡ እያንዳንዱ ሠንጠረዥ ግርጌ፡ ለየወሩ የተመደቡ ምንባቦች ተሰናድተዋል። እነዚህ ምንባቦች የተዘጋጁት፡ በሳምንቱ የሥራ ቀኖች፡ በየዕለቱ፡ ለጧትና ለማታ፡ እጅግ ቢያንስ፡ ኹለት ምዕራፎችን፥ እንዲሁም፡ በየሰንበቱ፥ በሌሎቹም፡ የበዓላትና የዕረፍት ጊዜያት፡ በተቻለ መጠን፡ ምዕራፎቹን ጨማምሮ በማንበብ፡ ከቃለ-እግዚአብሔር ዝክረ-ነገር ላለመራቅ እንደሚቻል በመገመት ነው። መዝሙረ ዳዊት፡ በየቀኑ፡ በጸሎት መልክ ስለሚደገም፡ በምንባቡ ውስጥ አልታከለም፤ አልተካተተም።*

*፮ኛ፦ ጾሙና ጸሎቱ፥ የሱባዔው ጭምር፥ ምንባቡም፡ በግል፥ በቤተሰብ፥ ወይም፡ በኅብረት በመሰባሰብ ሊካኼድ ይቻላል።*

፺ኛ፡- ይህን የቀን መቍጠሪያ፡ "አዳምና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" በሚል፡ ዓቢይ ርእስ ሥር፡ "አንደኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በጦብያ ፍለጋ!"፥"ኹለተኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውነት ፍለጋ!" እና "ሦስተኛ መጽሓፍ፡ ኢትዮጵያዊው፡ በእውቀት ፍለጋ!" ተብለው፡ ታትመው እየወጡ ያሉትን፥ እንዲሁም፡ በኢትዮጵያኛ እና በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ፡ «የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓተ ትምህርት፡ ለኢትዮጵያ ሕፃናት፤ "አንደኛ እና ኹለተኛ መጻሕፍት"» የሚል አርእስት ያላቸውን ዕትሞች፥ ደግሞም፡ "ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ፤ ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት።" ከእነዚህ በቀር፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" በሚል አጠቃላይ አርእስት ሥር፡ "አንደኛ መጽሓፍ"፥ "ኹለተኛ መጽሓፍ" እና "ሦስተኛ መጽሓፍ" ተብለው፡ በተከታታይ የወጡትን፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብለው፡ "ምናሴ፡ የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!"፥ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና Ethiopia: The Classic Case በሚሉ አርእስት፡ ታትመው የወጡትንና እየተሠራጩ ያሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን ዕትሞችና መጻሕፍት ለማግኘት፡ የኅዋ ሰሌዳችንን መጎብኘት፥ እንዲሁም፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።


**አሳታሚና አከፋፋይ**

Publisher & Distributor

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት**

**Ethiopia: The Kingdom of God**

**መልእክት ሣጥን ቍጥር፡ ፰፻፲፪።** P. O. Box 812

**ስልክና ዕምነቅ ቍ. 0፲፩-፬-፲፮-፲፰-፹፭ እና 0፲፩-፫-፳-00-፹፭** Tel. & Fax. 011-4-16-18-85 & 011-3-20-00-85

**አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ።** Addis Abeba, ETHIOPIA

**ወይም** or

**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**

**Tel.: 301-587-8074 ~ Fax.: 301-587-1971**

Email: info@ethkogserv.org

Web Site: www.ethkogserv.org

FaceBook: ethiopiathekingdomofgod


\+ \+ \+

## ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መስከረም ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Meskerem (Sept.-Oct., 2016). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ የድንግል ማርያምና 11<br>የኢየሱስ መሲሕ ልደታት። የኢትዮጵያ ነጻነት። ኪዳነ አዳም ወሔዋን። ቅዱስ ራጉኤል ሊቀ-መላእክት። ቅዱስ ዮሓንስ መጥምቅ። በርተሎሜዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት | ፪ 12<br>ዮሓንስ መጥምቅ | ፫ 13<br>ገዳማዊ አንበስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 14 | ፭ 15<br>ሄሮድስ የፈጃቸው ሕፃናት። የአሕመድ ግራኝን ወረራ፡ በሃይማኖት ጽናት ተቋቁሞ የተጋደለ፡ አጼ ንብለ-ድንግል | ፮ 16<br>ኢሳይያስ ነቢይ | ፯ 17<br>ኢትዮጵያዊቷ ኤልሣቤጥ፡ የመጥምቁ ዮሓንስ እናት። መናኔ-መንግሥት፡ አጼ ተክለ-ሃይማኖት |
| ፰ 18<br>ግዝረተ-ኢየሱስ | ፱ 19 | ፲ 20<br>አጼ መስቀል። ግማደ-መስቀሉ፡ በ፲፬ኛው ፻ ዓመት፡ በ፩ኛ አጼ ዳዊት፡ ወደኢትዮጵያ ስለገባ፡ "አጼ መስቀል" ተባለ | ፲፩ 21<br>አጼ በካፋ፡ ስመ-ጥሩው ምሁር መሪ | ፲፪ 22<br>ስለንስጥሮስ ኑፋቄ፡ የ፪፻ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኤፌሶን | ፲፫ 23 | ፲፬ 24 |
| ፲፭ 25 | ፲፮ 26<br>ኪዳነ-ኖኅ። ደመራ። (ለመስቀል በዓል ዋዜማ፡ ለችቦ እሳት የዛፍ አጣኖችን መደማመር) | ፲፯በዓለ 27<br>መስቀል። ኢየሱስ መሲሕ የተሠዋበት እውነተኛው መስቀል የተገኘበት | ፲፰ 28<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኤዎስጣቴዎስ ስለቅዳሜ ሰንበትነት ተከራክሮ የረታ | ፲፱ 29 | ፳ 30 | ፳፩ 1<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ዕርገት። የኢየሱስ መሲሕ ዜና መስቀል፡ በግሼን ማርያም የሚነገርበት |
| ፳፪ 2 | ፳፫ 3 | ፳፬ 4<br>ኪዳነ መልከ-ጼዴቅ | ፳፭ 5<br>ዮናስ ነቢይ። የክረምት (የዝናም) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 6<br>የመፀው (የጽጌ= የአበባ) ወራትና የጽጌ ማሕሌት መግቢያ | ፳፯ 7 | ፳፰ 8<br>ኪዳነ አብርሃም |
| ፳፱ የጽጌ ማሕሌት 9 | ፴ 10 | ማስታወሻ:- | | | | |

"ወፈለግ ይወጽእ እምቅድሜሁ፡ ከመ ይሥቅያ ለገነት፤ ወእምህየ ይትፈለጥ፡ ለአርባዕቱ መዓዝነ ዓለም። ...ወስሙ ለካልእ ፈለግ፡ 'ግዮን'፤ ወውእቱ ዘየዐውድ ኵሎ ምድረ-ኢትዮጵያ። ...ወነሥኦ እግዚአብሔር፡ ለዕጓለ-እመሕያው ዘገብሮ፤ ወሤሞ ውስተ ገነት፡ ከመ ይትገበራ፤ ወይዕቀባ። ገነትንም ያጠጣ ዘንድ፡ ከፊትለፊቱ፡ ወንዝ ይወጣ ነበር፤ ከዚያም፡ ወደአራቱ የዓለም ማዕዘኖች ይከፈላል። ...የኹለተኛውም ወንዝ ስሙ፡ 'ግዮን' ነው፤ እሱም፡ የኢትዮጵያን ምድር፡ ዙሮ የሚያጠጣ ነው። ...እግዚአብሔርም፡ የፈጠረውን ሰው ወስዶ፡ ያርሳት፥ ይቆፍራት፥ ይጠብቃትና ይንከባከባት ዘንድ፡ በገነት ላይ ሾሞ፡ በዚያ አኖረው።" [ዘልደት (ዘፍጥ.) ፪፥ ፰-፲፯።]

| | |
|---|---|
| የመስከረም ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘልደት [ዘፍጥ.] እና መጽሓፈ ጥበብ። |

## ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥቅምት ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of T'q'mt (Oct-Nov., 2016). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ 11 | ፪ 12<br>ገዳማዊ ሕርያቆስ፡ የቅዳሴ ማርያም ደራሲ | ፫ 13 | ፬ አብርሃ 14<br>ወአጽብሓ፡ የቅዱሱ ኪዳን ክርስትናን፡ በኢትዮጵያ ያስፋፉ አኀው አጼዎች | ፭ 15 |
| ፮ 16<br>ሓና ነቢይት፡ የነቢዩ ሳሙኤል እናት። ገዳማዊ ጳንጠሌዎን ከ፱ቱ ቅዱሳን። የጽጌ ማሕሌት | ፯ 17 | ፰ 18 | ፱ አጼ ዳዊት፡ 19<br>የጌታችን የኢየሱስ መሲሕን ግማደ-መስቀል፡ ከኢየሩሳ ሌም ያስመጣና "ዓባይን እገድባለሁ!" እያለ፡ በዚያ የሚኖሩ ክርስቲያኖችን፡ ከእስላሞች ጥቃት ያዳነ | ፲ ኢየሱስ መሲሕ 20<br>በ፫ ቀኑ፡በእናቱ ዕቅፍ ቤተ-መቅደስ የገባበት። በዓለ-ስምዖን። ሓና ነቢይት። አጼ ፋሲል፡ ካቶሊክነትን ተቃውሞ፡ ተዋሕዶነትን ያጸና | ፲፩ 21<br>የሕፃኑ ኢየሱስና የቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ስደት መታሰቢያ የጾሙ መግቢያ | ፲፪ 22<br>ወንጌላዊ ማቴዎስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት። ቅዱስ ድሜጥሮስ፡ የቀንና የዘመን አቈጣጠርን ያስተካከለ |
| ፲፫ 23<br>የጽጌ ማሕሌት | ፲፬ 24<br>ፊልጶስ ሓዋርያ፡ ኢትዮጵያዊዉን ጃንደረባ አቤሜሌክን ያጠመቀ። ገዳማዊ ዘሚካኤል አረጋዊ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን። ገብረ-ክርስቶስ | ፲፭ 25 | ፲፮ 26 | ፲፯ እስጢፋኖስ 27<br>ቀዳሚው ሰማዕት፡ የሹመቱ መታሰቢያ። ዲዮስቆሮስ ኢትዮጵያዊ፡ የግብፅ ሊቀ-ካህናትና የተዋሕዶ ሃይማኖት ተጋዳይ፥ የአኰቴት-ቍርባን ቅዳሴው ደራሲ | ፲፰ 28 | ፲፱ 29<br>አጼ ይምራሕ፡ ቀዳሚዎቹን የእስልምና ስደተኞች፡ በኢትዮጵያ አስተናግዶ የሸኘውና እነርሱ፡ "ነጋሽ" የሚሉት፡ ኪዳናዊው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ |
| ፳ 30<br>የጽጌ ማሕሌት | ፳፩ 31 | ፳፪ 1<br>ወንጌላዊው ሉቃስ | ፳፫ 2 | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 | ፳፮ 5 |
| ፳፯ 6<br>የጽጌ ማሕሌት | ፳፰ 7<br>አማኑኤል። ገዳማዊ ይማአታ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ:- | | |

"ወይቤሎ እግዚአብሔር አምላኩ ለኖኅ:- 'ጊዜሁ ለዕጓለ-እመሕያው፡ በጽሓ ቅድሜየ፡ እስመ መልአ ዐመፃ ዲበ ምድር እምኔሆሙ፤ ወናሁ አነ እደመስሶሙ እምድር። ...ባእ አንተ፥ ወኵሉ ቤትከ፡ ውስተ ታቦት፤ እስመ ኪያከ ረከብኩ ጻድቀ በቅድሜየ፡ በዛቲ ትውልድ። ...ወገብረ ኖኅ፡ ኵሎ ዘአዘዘ እግዚአብሔር አምላኩ። ...ወዐጸዋ እግዚአብሔር ለታቦት፡ እምአፍአሃ፤ ወኮነ ማየ አይኅ ላዕለ ምድር፡ ፵ መዓልተ፥ ወ፵ ሌሊተ፤ ወመልአ ማይ፤ ወአልዓላ ለታቦት፤ ወተለዓለት እምድር።" "እግዚአብሔር አምላኩ፡ ኖኅን፡ እንዲህ አለው:- 'በሰው ላይ፡ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ፡ በፊቴ ደረሰ! ከእነርሱ የተነሣ፡ በምድር ላይ የግፉ ጽዋ ሞልቷልና፤ እነሆ፡ እኔም፡ ከምድር አጠፋቸዋለሁ።...አንተን ግን፡ በዚህ ትውልድ መካከል፡ በፊቴ፡ እውነተኛ ሰው ኾነህ አግኝቼሃለሁና፡ አንተ፡ ከቤተሰብህ ኹሉ ጋራ፡ ወደመርከብ ግባ!' ኖኅም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ...እግዚአብሔርም፡ መርከቧን፡ በውጭ በኩል ዘጋት፤ በምድር ላይ፡ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት፡ የጥፋት ውኃ ዘነበ፤ ውኃውም መልቶ፡ መርክርቢቱን አንሳፈፋት፤ ምድርንም ለቀቀች።" የጥምቀት ምሳሌ ለኾነው፡ ለመጀመሪያው ሃይማኖታዊ ጉዞ፡ ቀይ ባሕርን አቋርጣ፡ አራራት ተራራ ላይ ለማረፍ፡ ከኢትዮጵያ ተነሣች። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፮፥ ፩-፲፫፤ ፯፥ ፩-፳፬።)

| | |
|---|---|
| የጥቅምት ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ሩት እና መጽሓፈ ሲራክ። |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ኅዳር ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of H'dar (Nov.-Dec., 2016). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | | | ፩ ነአኵቶ ለአብ፡10<br>መንግሥቱን፡በኢትዮጵ ያዊው የመልከ-ጼዴቅ ሥርዓት የመራ አጼ | ፪ 11 | ፫ 12 |
| ፬ 13<br>የጽጌ ማሕሌት ፍጻሜ | ፭ ለንጊኖስ፡ 14<br>ጌታ ተሰቅሎ ሣለ፡ ጎኑን፡ በጦር የወጋና ኋላ አምኖ፡ በሰማዕ ትነት የተጋደለ። የስደት ጾም ማብቂያ | ፮ ቊስቋም: 15<br>ሕፃኑ ኢየሱስ እና ቅድስት እናቱ፡ በስደት የቆዩባት የኢትዮጵያ ገዳም መታሰቢያ በዓል | ፯ 16 | ፰ 17<br>አርባዕቱ እንስሳ። መንበረ ሥላሴን የሚሸ ከሙ ሕያዋን ፍጡራን (፬ቱ:- ሰው፥ ላሕም፥ አንበሳና ንሥር) | ፱ 18<br>ስለአርዮስ ኑፋቄ፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤ፡ በኒቅያ | ፲ 19 |
| ፲፩ 20<br>ቅድስት ሓና ኢትዮጵያዊት: የድንግል ማርያም እናት | ፲፪ 21<br>ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ-መላእክት። አጼ በእደ-ማርያም፡ ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፲፫ 22<br>አእላፍ መላእክት | ፲፬ 23<br>በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. በደርግ የዓመፅና የክህደት አገዛዝ፡ በኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ላይ የግፍ ግድያ ተፈጸመ | ፲፭ 24 | ፲፮ 25<br>የጾመ-ነቢያት መግቢያ | ፲፯ 26<br>አዲስ አበባ ከተማ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. የተቈረቈረችበት |
| ፲፰ 27<br>ፊልጶስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ ኪዳነ ሙሴ30<br>ሕፃን ማርያም፡ በ፫ ቀኗ፡ በቤተ መቅደስ በጌታ ፊት የቀረበችበት። ማርያም ጽዮን። ማክዳ ንግሥት እና ልጇ ምኒልክ | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ቆርነሌዎስ ጻድቅ (የሓዋ. ምዕ. ፲) | ፳፬ 3<br>፳፬ቱ ካህናተ-ሰማይ |
| ፳፭ 4<br>መርቆሬዎስ ሰማዕት | ፳፮ 5<br>በናግራን (የመን)፡ ኢትዮጵያውያን/ያት ሰማዕታት። በዚያ፡ የአጼ ካሌብ ድል። ኢየሱስ-ሞዐ ዘሓይቅ | ፳፯ 6<br>ገዳማዊ ሊቃኖስ ኢትዮጵያዊ፡ ዘደብረ-ቊንጽል። | ፳፰ 7<br>ገዳማዊ ሊቃኖስ፡ከ፱ኙ ቅዱሳን | ፳፱ 8<br>የሊቀ ሓዋርያት ጴጥሮስ ደቀ-መዝሙር፡ ቀሌምንጦስ። የሰማዕታት መጨረሻ ጴጥሮስ | ፴ ገብረ መስቀል9<br>(አጼ) በዘመኑ የቅዱስ ያሬድ ሙያና የ፱ኙ ቅዱሳን ዜና የገነነበት የጾመ-ነቢያት ማብቂያ | ማስታወሻ:- |

"ወመልከ-ጼዴቅ አምጽአ ኅብስተ፥ ወወይነ፤ ወካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል፤ ወንጉሠ ሳሌም ውእቱ። ወባረኮ ለአብራም፤ ወይቤሎ:- 'ቡሩኩ አብራም ለእግዚአብሔር ልዑል፣ ዘፈጠረ ሰማየ ወምድረ! ወቡሩክ እግዚአብሔር ልዑል፡ዘአግብአ ለጸላእትከ፡ ውስተ እዴከ! ወወሀቦ አብራም፡ ዐሥራተ ዕድ፡ እምኵሉ።' መልከ-ጼዴቅም፡ የኅብስትና የወይኑን ቍርባን አመጣ፤ እርሱም፡ የገናናው እግዚአብሔር አገልጋይ፥ የሳሌምም ንጉሥ ነው። አብራምንም:- 'አንተ፡ ሰማይንና ምድርን ለፈጠረው፡ ለገናናው እግዚአብሔር የተባረክህ ነህ! ጠላቶችህን፡ በእጅህ የጣለልህ ገናናው እግዚአብሔር የተመሰገነ ነው!' ብሎ ባረከው። አብራምም፡ ከገንዘቡ ኹሉ፡ አሥራትን ሰጠው።" የእስራኤል ልጆች አባት የኾነውን፡ አብርሃምን፡ ለመለኮታዊው የግርዛት ቃል ኪዳን ያበቃው፡ የኢትዮጵያ ልጆች አባት የኾነው፡ የዚህ፡ የኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ የክህነት አገልግሎትና ቡራኬ መኾኑን ማስተዋል ነው። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፬፥ ፲፯-፳።)

| የኅዳር ወር ምንባብ:- | ኦሪት ዘፀአት እና ትንቢተ ኤርምያስ። |
|---|---|

## ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ታኅሣሥ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Tah'sas (Dec., 2016-Jan, 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሐሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ ከተራ 8<br>ለጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ ውኃ፡ ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት።<br>የጋድ ጾም | ማስታወሻ፡- | | | | | ፩ በዓለ ትስብእት 10<br>ኢየሱስ መሲሕ የተፀነሰበት።<br>ብሥራተ-ገብርኤል።<br>ኤልያስ ነቢይ።<br>ቤትሳባ ኢትዮጵያዊት፡ የሰሎሞን እናት |
| ፪ 11 | ፫ ሕፃን ማርያም 12<br>በሰእለት፡ ለቤተ-መቅደስ የተሰጠችበት። ቅዱስ ፋኑኤል ሊቀ-መላእክት። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ። ሀብተ-ጊዮርጊስ፡ አባ መላ | ፬ 13<br>እንድርያስ፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት | ፭ 14 | ፮ በ፲፱፻፴፫ 15<br>ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን የተሠየፉት የአዲስ ዓለም ማርያም ሰማዕታት ካህናት | ፯ 16<br>ፅንሰታ ለማርያም (ድንግል ማርያም የተፀነሰችበት) | ፰ 17<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ኪሮስ |
| ፱ 18<br>ስብከት።<br>ገዳማዊ በአሚን ኢትዮጵያዊ | ፲ በወሎ፡ 19<br>ደብረ-እግዚአብሔርና የሓይቅ መካነ-እስጢፋኖስ፡ በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት። | ፲፩ 20 | ፲፪ 21<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ ሳሙኤል፡ የዋልድባው | ፲፫ 22 | ፲፬ በ፲፱፻፳፰ 23<br>ዓ.ም. የፋሺስት ጣልያን አየር ኃይል፡በኢትዮጵያ ላይ፡ የመርዝ ጢስ ማዝነብ ጀመረ | ፲፭ 24 |
| ፲፮ 25<br>ብርሃን | ፲፯ 26 | ፲፰ 27<br>በአኵስሙ ሊቀ-ካህናት እንበረም ተልኮ ያልታሰበውን የግብፅን የጵጵስናን አገዛዝ ወደኢትዮጵያ ያመጣ አባ ሰላማ | ፲፱ 28<br>ቅዱስ ገብርኤል፡ ፫ቱ ደቂቅን፡ ከባቢሎን እሳት ያዳነበት | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 |
| ፳፫ 1<br>ኖላዌ።<br>ኪዳነ ዳዊት | ፳፬ 2<br>የእቲሳው እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት ልደት | ፳፭ 3<br>የመፀው (የጽጌ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የሐጋይ (የበጋ) ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>አጼ ኢያሱ፡ ብርሃን ሰገድ | ፳፰ 6 | ፳፱ 7 |

ኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ ከባረከው በኋላ፡ እግዚአብሔር ተገልጦለት፡ "አነ ውእቱ እግዚአብሔር ፈጣሪከ፡ ዘሖርኩ ቅድሜከ! አሥምር ቅድሜየ! ወኩን ንጹሐ! ወእሠይም ኪዳነ፡ ማእከሌየ ወማእከሌከ! ወአብዝኀከ ጥቀ! ...ወኢይሰመይ እንከ ስምከ 'አብራም'፤ አላ፡ 'አብርሃም' ይሰመይ! እስመ አበ ብዙኃን አሕዛብ ረሰይኩከ። በፊትህ የኼድሁ ፈጣሪህ እግዚአብሔር፡ እኔ ነኝ! በፊቴ፡ በጎ ነገር አድርግ! ንጹሕ ኹን! በእኔ እና በአንተ መካከል ኪዳንን እሠይማለሁ! እጅግም አበዛሃለሁ!...እንግዴህም፡ ስምህ፡ 'አብራም' አይባልም፤ 'አብርሃም' እንጂ። ለብዙዎች አሕዛብ፡ አባት አድርጌሃለሁና።" ያለው፡ ይህ የሃይማኖትና የምግባር ሰው፡ ከተገረዘና ሣራ ከሞተች በኋላ፡ ኢትዮጵያዊቷን ኬጡራን፡ በሚስትነት አግብቶ፡ "ምድያማውያን" የተባሉ፡ የኢትዮጵያን ልጆች በመውለዱ፡ ለኢትዮጵያዊነት፡ አንዱ አብነት ኾኗል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፲፯፥ ፩-፭፤ ፳፤፳፭።)

| | |
|---|---|
| የታኅሣሥ ወር ምንባብ፡- | መጽሐፈ ሳሙኤል እና ትንቢተ ሕዝቅኤል። |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ጥር ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of TT'rr (Jan.-Feb., 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:-<br>ታኅሣሥ<br>፴ ከተራ፡ 8<br>ለጥምቀት በዓል ዋዜማ፡ ውኃ፡ ከወንዝ ተወስዶ የሚከተርበት።<br>[የገሀድ ጾም] | ፩ ጥምቀት 9<br>በዓለ አስተርእዮ<br>ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አቤሜሌክ [ባኮስ]። በቅዳሴ ጸሎቱ፡የጥምቀት ወንዝ የቆመለት የተጕለቱ ታቦት ዋሻ ካህን፡ ትልቁ ወልደ-ኢየሱስ | ፪ 10<br>አቤል ጻድቅ | ፫ 11<br>ገዳማዊ መጣዕ ዘሊባኖስ ኢትዮጵያዊ | ፬ 12<br>ወንጌላዊ ዮሓንስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት | ፭ 13 | ፮ 14<br>ኖኅ።<br>ዕርገተ ኤልያስ |
| ፯ 15<br>የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ | ፰ 16 | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20<br>ድንግል ማርያም፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻት፥ ልጇም ኢየሱስ፡ እውነተኛው መሲሕ መኾናቸው የተገለ ጠበት የቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል | ፲፫ 21<br>በ፴፩ ዓ.ም. በዘመነ በጃንደረባዋ አማካ ይነት፡ክርስትና ወዳገርዋ የመጣላት፡ ሕንደኬ፡ ንግሥተ-ኢትዮጵያ |
| ፲፬ እንበረም 22<br>ሊቀ-ካህናት ዘአኵስም በ፫፻፳፭ ዓ.ም. የኢት ዮጵያን ሥርዓተ-ቤተ ክርስቲያን ያሟላ | ፲፭ 23<br>ቂርቆስ፡ የ፫ ዓመት ሕፃን ሰማዕት | ፲፮ 24<br>ኢየሉጣ ሰማዒት፤ የሕፃኑ ቂርቆስ እናት | ፲፯ እስጢፋኖስ 25<br>እንደጌታው፡ኢየሱስ መሲሕ፡ለእውነት፡በይፋ መስክሮ የተሠዋ ቀናዒ ካህንና ቀዳሚ ሰማዕት | ፲፰ 26<br>ዝርወተ ዐፅሙ ለጊዮርጊስ | ፲፱ 27 | ፳ 28 |
| ፳፩ መርዓዊ 29<br>የቅድስት ድንግል ማርያም ፍልሰተ ወደገነት | ፳፪ 30 | ፳፫ 31 | ፳፬ 1 | ፳፭ 2 | ፳፮ 3 | ፳፯ 4<br>ዕርገተ-ሄኖክ |
| ፳፰ 5<br>የበዓለ-ኢትዮጵያ መግቢያ | ፳፱ 6 | ፴ የበዓለ 7<br>ኢትዮጵያ ማብቂያ | ማስታወሻ:- | | | |

ሙሴ፡ከግብፅ፡ በስደት፡ ወደኢትዮጵያ መጥቶ፡ ስለኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያዊው ካህን፡ ከዮቶር ተምሮ፡ ካመነ በኋላ፡የካህኑን ሴት ልጅ፡ ሲጳራን አገባ፤ የአማቱን በጎች ሲጠብቅ ሣለም፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ተልጸለት፡ ያዘዘውን ኹሉ በመፈጸሙ፡ ኢትዮጵያዊነትን መቀበሉ፡ እውን ኾኗል። ከዚህ ኢትዮጵያዊነቱ የተነሣም፡ የኋላ ኋላ፡ በወንድሙና በእኅቱ ሳይቀር፡ ከእስራኤል ሕዝብ፡ በደል እንደደረሰበት ተጽፏል። መሴና የእስራኤል ሕዝብ፡ ገና፡ በምድረ-በዳ ሠፍረው ሣሉ፡ የሚቃጠልንና ሌላ መሥዋዕትን፡ ለእግዚአብሔር በማቅረብ፡ ሥርዓተ-ክህነትን፥ ስለሕዝብ አስተዳደርና ስለፍትሕ አሰጣጥም በማስተማር፡ የኢትዮጵያን እግዚአብሔራዊ ሥርዓተ-መንግሥት፡ አማቱ፡ ኢትዮጵያዊው ዮቶር፡ ለሙሴና ለአሮን፥ ለሕዝቡ ሽማግሌዎችም ኹሉ ማሳየቱ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግቧል። (ዘጸአ. ፫፥ ፩-፭፤ ፲፰፥ ፩-፳፯። ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፭።)

| | |
|---|---|
| የጥር ወር ምንባብ:- | መጽሓፈ ኢዮብ እና የማቴዎስ ምሥራች። |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ የካቲት ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Yekkatit (Feb.-Mar., 2017. Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቀዳሚት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | ፩ 8<br>ስለመቅዶንዮስ ኑፋቄ የ፫፻ ሊቃውንት ጉባኤ በቍስጥንጥንያ | ፪ 9 | ፫ የግሼን ማርያም 10<br>አምባ፡ በ፲፭፻፴፪ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተመዘበረበት | ፬ ጣይቱ 11<br>ብጡል፡ ብርሃን ዘኢትዮጵያ |
| ፭ 12<br>ዘወረደ<br>(ቅበላ) | ፮ የዓቢይ 13<br>ጾምና የጾመ ሕርቃል መግቢያ። ማርያም እንተ ዕፍረት፤ ጌታን፡በእንባዋ እግሩንያጠበች | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16 | ፲ 17<br>ያዕቆብ ወልደ-እልፍዮስ፤ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት | ፲፩ 18 |
| ፲፪ ቅድስት19<br>በ፲፱፻፳፱ዓ.ም.የፋሺስት ጣልያን ጦር፡ በሰላማዊው የአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግድያ | ፲፫ 20<br>የጌታ የአርባ ቀን ጾም መነሻ | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23<br>ኪዳነ-ምሕረት፡ በድንግል ማርያም እና በኢየሱስ መሲሕ ተገኘ! | ፲፯ 24 | ፲፰ 25<br>አዝማች ደገልሓን፤ የአሕመድ ግራኝን ጦር፡ በቆራጥነት የተዋጋ ጀግና ኢትዮጵያዊ |
| ፲፱ 26<br>ምኵራብ። | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>ከይሁዲቷ ጉዲት አገዛዝ በኋላ፡ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. በአገዉ (በዛጔው) መርሓ-ተክለ ሃይማኖት፡ የኢትዮጵያ መልከ ጼዴቃዊ ሥርዓተ-መንግሥት ተመለሰ | ፳፪ 1 | ፳፫ 2<br>ኢትዮጵያ፡ ኃይሏ፡በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት፡ የአድዋ ድል | ፳፬ 3 | ፳፭ 4 |
| ፳፮ 5<br>መጻጕዕ። | ፳፯ ግራኝ 6<br>አሕመድ፡ በ፲፭፻፴፭ ዓ.ም. ድል ኾነ | ፳፰ 7 | ፳፱ 8 | ፴ 9 | ማስታወሻ፡- | |

"ይሁዳ፡ ዕጓለ-አንበሳ! እምኆዝአትከ ዕርግ! ወልድየ! ሰከብከ፤ ወኖምከ፡ ከመ አንበሳ፥ ወከመ ዕጓለ-አንበሳ፡ አልቦ ዘያነቅሐከ። ኢይጠፍእ ምልክና፡ እምይሁዳ፤ ወምስፍና፡ እምአባሉ፣ እስከ አመ ይረክብ፡ ዘጽኑሕ ሎቱ። ወውእቱ፡ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ። ...ወብዙኃን እለ በከዩ፤ ወአነሂ ምስሌሆሙ፤ እስመ አልቦ ዘተረክበ፡ ዘይደልዎ ይክሥታ፥ ወይርአያ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፡ [እንተ ሀለወት] ውስተ የማኑ፡ ለውእቱ፡ዘይነብር ዲበ መንበር። ወይቤለኒ፡ አሓዱ፡ እምውስተ እልክቱ [፳፬ቱ] ሊቃናት፡- 'ኢትብኪ! ናሁ፡ ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ እምውስተ ሥርዉ ለዳዊት፤ ከመ ይፍትሓ፡ ለይእቲ መጽሓፍ፥ ወለማኅተሚሃ!' የይሁዳ አንበሳ ደቦል! ከመደብህ ውጣ! ልጄ! እንደአንበሳ ተኛህ፤ አንቀላፋህም፤ እንደአንበሳ ደቦልም፡ ሊቀሰቅስህ የሚችል የለም። መንግሥት፡ ከይሁዳ፥ የሕዝብ አስተዳደርም፡ ከወገኑ አይወጣም፤ ይህ ሥልጣን፡ የሚጠበቅለትን፣ ለአሕዛብም ተስፋቸው የኾነውን፡ እርሱን እስከሚያገኝበት ጊዜ ድረስ። ...በዙፋኑም ላይ በተቀመጠው፡ በቀኝ እጁ ያለችውን መጽሓፍ ሊዘረጋ፥ ሊመለከታትም የሚገባው፡ ማንም ስላልተገኘ፡ ብዙዎች አለቀሱ፣ እኔም ዐብሬአቸው አለቀስሁ። ከእነዚያ [ከ፳፬ቱ] ሊቃናት መካከል፡ አንዱ፡- 'አታልቅስ! እነሆ፡ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፤ እርሱም፡ የዳዊት ሥር፡ መጽሓፏን ይዘረጋ ዘንድ፥ ማኅተሟንም ይፈታ ዘንድ፡ ድል ነሥቷል!' አለኝ።" የሚለውን፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ በምግባር ስለፈጸሙት፡ እውነተኞቹ እስራኤል እነርሱ መኾናቸው ተረጋግጧል። (ዘልደት [ዘፍጥ.] ፵፱፥ ፱-፲፤ ራእ. ፭፥፩-፭።)

| | |
|---|---|
| የየካቲት ወር ምንባብ፡- | ኦሪት ዘዳግም፥ ትንቢተ ዮናስና የማርቆስ ምሥራች። |

## ፳፻፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ መጋቢት ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Meggabit (Mar.-Apr., 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ Sunday | ሰኞ Monday | ማግሰኞ Tuesday | ረቡዕ Wednesday | ሐሙስ Thursday | ዓርብ Friday | ቅዳሜ Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | | ፩ 10<br>አጼ ዮሐንስ ፬ኛ፡ የመተማው ሰማዕት በድርቡሽ እስላም ወራሪ ተሠየፈ | ፪ 11 |
| ፫ 12<br>ደብረ ዘይት | ፬ 13 | ፭ ገብረ 14<br>መንፈስ ቅዱስ | ፮ 15 | ፯ 16 | ፰ 17<br>ማትያን፡ ከ፲፪ቱ ሐዋርያት | ፱ 18 |
| ፲ 19<br>ገብር ኄር | ፲፩ 20<br>ገዳማዊ አሌፍ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን | ፲፪ 21 | ፲፫ 22 | ፲፬ 23 | ፲፭ 24 | ፲፮ 25 |
| ፲፯ 26<br>ኒቆዲሞስ | ፲፰ 27 | ፲፱ 28 | ፳ 29 | ፳፩ 30 | ፳፪ 31 | ፳፫ 1<br>ዳንኤል ነቢይ |
| ፳፬ 2<br>ሆሣዕና<br>ንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ | ፳፭ 3<br>የሰሙነ ሕማማት መግቢያ።<br>የሓጋይ (የበጋ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 4<br>የጸደይ (የበልግ) ወራት መግቢያ | ፳፯ 5<br>አጼ ገላውዴዎስ፡ ኵትልክናን፡ በተዋሕዶነት የተቋቋመና በእስላም ወራሪ፡ ሰማዕትነትን የተቀበለ | ፳፰ 6<br>ጸሎተ ሓሙስ።<br>ቈስጠንጢኖስ ንጉሥ፡ ስለሃይማኖትና ስለፍትሓ-ነገሥት ዝግጅት፡ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ጉባኤን፡ በኒቅያ ያሰባሰበ | ፳፱ 7<br>የኢየሱስ መሲሕ መስቀለ-ሞቱ | ፴ 8<br>ኢየሱስ መሲሕ በመቃብር ያረፈባት ሰንበት |

"'ናሁ ይመጽእ መዋዕል!' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወአቀውም ለዳዊት፡ ሠርፀ ጽድቅ፤ ወይነግሥ ንጉሥ፡ ዘይኄሊ፤ ወይገብር ጽድቀ፥ ወርትዐ፡ በዲበ ምድር። ...ወይሠርፅ ጽድቅ፡ በመዋዕሊሁ፤ ወብዙኀ ሰላም፡ እስከ የኀልፍ ወርኅ። ወይኴንን እምባሕር፡ እስከባሕር፤ ወእምአፍላግ፡ እስከአጽናፈ ዓለም። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፤ ወጸላእቱሂ፡ ሐመደ ይቀምሑ። ...እግዚአብሔርሰ፡ ንጉሥ ውእቱ፡ እምቅድመ ዓለም፤ ወገብረ መድኃኒተ በማእከለ ምድር። ...አንተ ሰበርከ ርእሶ፥ ወቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ። ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ፡ ለሕዝበ ኢትዮጵያ። 'እነሆ፡ ለዳዊት፡ የእውነት ቍጥቋጥ የማስነሣበት ጊዜ ይመጣል! እርሱም፡ በምድር ላይ፡ እውነትንና ቅንነትን የሚያስብና የሚያደርግ ንጉሥ ይኾናል!' ይላል እግዚአብሔር። ...በዘመኑ፡ እውነት ትከሠታለች፤ የግብዝነቱም ወራት አልፎ፡ ሰላም ይበዛል። ከባሕር እስከባሕር፥ ከታላላቁ ወንዞች፡ እስከምድር ዳርቻ ያለውን ዓለም ያስተዳድራል። የኢትዮጵያ ልጆች፡ ዜጎቹ ይኾናሉ። ጠላቶቹም፡ አፈር ይበላሉ። ...እግዚአብሔርማ፡ ከዓለም አስቀድሞ፡ ንጉሥ ነው! በምድርም መካከል፡ መድኃኒትን አደረገ። ...አንተ፡ የእባቡን ራስ ሰበርህ! ራሶቹንም፡ ቀጠቀጥህ! ለኢትዮጵያ ሕዝብህም፡ ሲሳያቸውን ሰጠሃቸው!(ኤር. ፳፫፥ ፭። መዝ.፸፩፥ ፯-፱፤ ፸፫፥ ፲፪-፲፬)

| | |
|---|---|
| የመጋቢት ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ-ኢሳይያስ እና የጳውሎስ መልእክታት። |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመት-ምሕረት ወርኀ ሚያዝያ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Miazia (Apr.-May, 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 9<br>የኢየሱስ መሲሕ በዓለ ትንሣኤ | ፪ ማዕዶት 10<br>(በሕይወተ-ሥጋ እያሉ፡ በመንፈስ፡ ወደትንሣኤ ሕይወት መሻገር) | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ አዳም ሓሙስ 13<br>(የ፭ሺ፭፻ው ዓመት ተስፋ ፍጻሜ ዝክር። ሕዝቅኤል ነቢይ | ፮ 14<br>ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ፡ አርበኛው መሪ | ፯ 15<br>ኢትዮጵያዊው ኢያቄም፡ የድንግል ማርያም አባት |
| ፰ ዳግም ትንሣኤ16<br>ከፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ በኋላ ያለው የፍጻሜ ትንሣኤ መታሰቢያ። ማርቆስ ወንጌላዊ | ፱ 17 | ፲ 18 | ፲፩ 19 | ፲፪ 20<br>ደብረ-ብርሃን፡ በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ የተቃጠለበት | ፲፫ 21<br>በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ፋሺስት ጣልያን፡ ማኅበረ ሥላሴን፡ በአየር ኃይሉ የደበደበበት | ፲፬ 22 |
| ፲፭ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. 23<br>ሦስት የማኅበረ-ሥላሴ ገዳም አባሎች፡ በፋሺስት የጣሊያን ጦር የተገደሉበት | ፲፮ 24 | ፲፯ 25<br>ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ:ከ፲፪ቱ ሐዋርያት | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 | ፳ 28 | ፳፩ 29<br>እጨጌ ዕንባ ቆም፡ ሰባኬ ሃይማኖት |
| ፳፪ 30 | ፳፫ 1<br>ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት | ፳፬ 2 | ፳፭ 3<br>ርክበ ካህናት | ፳፮ 4 | ፳፯ ኢትዮጵያ 5<br>ነጻነቷና በፋሺስት ጣልያን ላይ የተቀዳጀ ችው ድል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ መኾኑ የተረጋገጠበት | ፳፰ 6 |
| ፳፱ 7 | ፴ 8 | ማስታወሻ፡- | | | | |

"ወንግሥተ ሳባ፡ ሰምዓት ስሞ ለሰሎሞን፣ ወስሞ ለእግዚአብሔር፤ መጽአት ትፍትኖ፡ ምስለ ጥበባ። ወቦአት ኢየሩሳሌም፡ በኃይል ክቡድ ፈድፋደ። ...ወቦአት ኀበ ሰሎሞን፤ ወተናገረቶ ኵሎ ዘሀሎ ውስተ ልባ። ...ወወሀበቶ ለሰሎሞን፡ ምእተ፥ ወዕሥራ መካልየ ዘወርቅ፥ ወአፈዋተ ፈድፋደ ብዙኀ፥ ወዕንቈ ክቡረ፤ ወአልቦ አመ መጽአ ብዙኀ አፈዋተ፡ ዘከመ አሜሃ፡ ዘወሀበት ንግሥተ ሳባ፡ ለሰሎሞን። የሳባ ንግሥት፡ የሰሎሞንን ስም፥ የእግዚአብሔርም ስም፡ በእርሱ ሲጠራ በሰማች ጊዜ፡ ስለሃይማኖቱና ስለእውነተኛ ማንነቱ፡ በጥበቧ ትፈትነው ዘንድ፡ እጅግ ብዙ ከኾነ ሠራዊትና ጓዝ ጋር፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደኢየሩሳሌም መጣች። ...ወደሰሎሞንም ገባች፤ በልቧ ውስጥ ያለውን ኹሉ፡ ገልጣ ነገረችው። መቶ ሃያ የወርቅ መክሊትን፥ እጅግ ብዙ የኾነ ሽቱን፥ የከበረ ዕንቍንም [ሉልን] ሰጠችው። የዚያን ጊዜ፡ የሳባ ንግሥት፡ ለሰሎሞን የሰጠችውን፡ ያን የመሰለ ብዛት ያለው ስጦታ፡ ከዚያ ወዲያ አልመጣም።" የትንቢቱ ፍጻሜና ዘላለማዊው ንጉሥ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይ በተገለጠበት ጊዜ፡ ከእርሱ፡ ማስረጃ ምልክትን ለጠየቀው፡ ለዚያ፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ ክፉና ዘማዊ ትውልድ፡ እንዲህ የሚል የመጨረሻ መልስን ሰጠ፡- "ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ፡ አመ ዕለተ ደይን፡ ምስለ ዛ ትውልድ፤ ወትትፋትሓ፥ ወታስተኃፍራ፤ እስመ መጽአት እምአጽናፈ ምድር፡ ትስማዕ ጥበቢሁ ለሰሎሞን፤ ወናሁ፡ ዘየዐቢ እምሰሎሞን፡ ሀሎ ዝየ። ንግሥተ አዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ፡ ትፋረደዋለች፤ ታሳፍረዋለችም። የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት፡ ከምድር ዳር መጥታለችና። እነሆም፡ ከሰሎሞን የሚበልጥ፡ ከዚህ አለ።" ከዚህ ፍርድ ለመዳን፡ "ነገሥተ ምድር ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር! ወዘምሩ ለአምላክነ! ወለኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር። እናንተ፡ በምድር ያላችሁ የሰዎች መንግሥታት ኹሉ፡ ለፈጣሪያችሁ ለእግዚአብሔርና እጇቿን፡ ወደእርሱ ዘርግታ ለምትኖረው፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘምሩ! ምስጋናችሁንም አቅርቡ!" (፩ነገ. ፲፥ ፩-፲። ማቴ. ፲፪፥ ፵፪። መዝ. ፷፯፥ ፴፩-፴፪።)

| የሚያዝያ ወር ምንባብ፡- | ትንቢተ ዳንኤል እና ራእየ-ዮሓንስ። |
|---|---|

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ግንቦት ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of G'nbot (May-June, 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሐሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ቅዳሜ<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ:- | | ፩ ቅድስት 9<br>ድንግል ማርያም፡ በሊባኖስ ተራራ ላይ የመወለዷ መታሰቢያ | ፪ 10<br>ኢዮብ ጻድቅ ኢትዮጵያዊ | ፫ 11 | ፬ 12 | ፭ 13<br>ኢትዮጵያውያኑ፡ ኤርምያስ ነቢይ፥ ደቀ-መዛሙርቱ፡ አቤሜሌክና ባሮክ |
| ፮ 14<br>የደብረ ሊባኖሷ ቅድስት ሰሎሜ፡ ኢትዮጵያዊት | ፯ 15 | ፰ 16 | ፱ 17<br>ዕሌኒ ንግሥት፡ የጌታን መስቀል አስቆፍራ ያስገኘች | ፲ ዕርገት 18<br>በሃይማኖታቸው ጽናት፡ ከባቢሎን እሳት የዳኑት፡ አናንያ፥ አዛርያና ሚሳኤል | ፲፩ ያሬድ 19<br>ኢትዮጵያዊው ማሕሌታይ ካህን። ገዳማዊ አሴር፡ የባሌ መምህር | ፲፪ አጼ 20<br>እስክንድር፡ የእስላምን ወራሪ ጦር ሲከላከል፡ ሰማዕትነትን፡ በወጣትነቱ የተቀበለ። ዮሓንስ አፈወርቅ |
| ፲፫ 21<br>የደብረ-ሊባኖስ ገዳም አባሎች፡ በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር የተሠዉበት | ፲፬ 22 | ፲፭ 23<br>ናትናኤል፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት | ፲፮ 24 | ፲፯ 25 | ፲፰ 26 | ፲፱ 27 |
| ፳ በዓለ 28<br>**መንፈስ ቅዱስ**<br>(በዓለ ሃምሳ)<br>ቅዱስ አጼ ካሌብ፡ ወደ ናግራን (የመን) ግዛቱ፡ በመርከብ ዘምቶ፡ የአይሁድን አሠቃቂ ወረራ ድል ያደረገበት | ፳፩ 29<br>የሓዋርያት ጾም መግቢያ<br><br>የደርግ፡ የክህደትና የዓመፅ አገዛዝ፡ በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. የተወገደበት | ፳፪ 30 | ፳፫ 31<br>የጾመ- ድኅነት (የረቡዕና ዓርብ ጾም) መነሻ | ፳፬ 1<br>ዕንባቆም ነቢይ | ፳፭ 2<br>ቅድስት ሰሎሜ፡ በሕፃኑ ኢየሱስና በቅድስት ድንግል እናቱ ስደት ያልተለየች | ፳፮ 3<br>ቶማስ፡ ከ፲፪ቱ ሓዋርያት |
| ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>ገዳማዊ አፍጼ እና ገዳማዊ ጉባ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን | ፴ 7 | ማስታወሻ:- | | |

ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ወደመቅደስ ወጥቶ ሲያስተምር፡ ሊገድሉት ለሚፈልጉት አይሁድ፡ "ኢትፍትሑ፡ በአድልዎ ገጽ! አላ፡ ፍትሐ-ጽድቅ ፍትሑ! ቅን ፍርድን ፍረዱ እንጂ፡ መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" አላቸው። ለምን እንዲህ አላቸው? "መልክን አይታችሁ አትፍረዱ!" የሚለው የጌታ ቃል፡ ቀድሞ፡ በሙሴ ላይ፡የተነሣሣባቸው ቅንዓት የተከሠተው፡ በኢትዮጵያዊት ሚስቱ፡ በሲጳራ ምክንያት እንደነበረ ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በእርሱ፡ በኢየሱስ መሲሕ ኢትዮጵያዊነት ላይ የተቀጣጠለ መኾኑን ሲያመለክታቸው እንደኾነ፡ ማስተዋል ነው። "'አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ። ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ ‹የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።› አለ።" ሲል፡ ነቢዩ አሞጽ የተናገራቸውን ቃላት፡ በዚያን ጊዜም፡ አይሁድ አላስተዋሏቸውም። (ዮሐ. ፯፥ ፲፬-፳፬። ዘኍል. ፲፪፥ ፩-፲፮። አሞ. ፱፥ ፯።)

| | |
|---|---|
| የግንቦት ወር ምንባብ:- | መጻሕፍተ አስቴር፥ ምሳሌ እና መክብብ። |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሰኔ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Seney (June-July, 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | | | | ፩ ወንድሞቹ የሸጡት 8<br>የያዕቆብ ልጅ፡ ዮሴፍ እና ኢትዮጵያዊት ሚስቱ አስናት | ፪ 9 | ፫ 10 |
| ፬ 11 | ፭ 12 | ፮ በፋሺስት ጣልያን የታጠቀ 13<br>የተመራም፡ የራያ እስላም፡ በ፲፱፻ ፳፱ ዓ.ም. የሸዋ ቆላ ኢትዮጵያውያንን፡ በሰለባ ጭምር የፈጀበት | ፯ 14 | ፰ 15 | ፱ 16<br>ሳሙኤል ነቢይ | ፲ 17 |
| ፲፩ 18 | ፲፪ 19<br>**ቅዱስ ሚካኤል**<br>ሊቀ-መላእክት።<br>**አጼ ላል-ይበላል** | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22 | ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ገዳማዊ ገሪማ፡ ከ፱ኙ ቅዱሳን |
| ፲፰ 25 | ፲፱ 26 | ፳ ሕንጸታ፡ በአዳምና 27<br>ሔዋን ኪዳነ ሰብሳብ: በኢትዮጵያ የተመሠረተችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በኢየሱስ መሲሕና በድንግል ማርያም ኪዳነ-ምሕረት: በኢየሩሳሌም ተገለጠች። ኤልሳዕ ነቢይ | ፳፩ 28<br>በቅዱሱ ኪዳን ላይ ክህደትና ዓመፅ የፈጸመውን የኢትዮጵያ ትውልድ ሊቀጣ የተላከው ደርግ በ፲፱፻፳፮ ዓ.ም. የተቋቋመበት | ፳፪ 29 | ፳፫ 30<br>**ሰሎሞን ንጉሥ የምኒልክ አባት** | ፳፬ 1<br>**ሙሴ**<br>(ጸሊም)<br>ኢትዮጵያዊ |
| ፳፭ 2<br>ያስቆሮቱ ያይደለ ሓዋርያው ይሁዳ የጌታ ዘመድ።<br>የጸደይ (የበልግ) ወራት ማብቂያ | ፳፮ 3<br>ኢያሱ ወልደ-ነዌ።<br>የክረምት (የዝናም) ወራት መግቢያ | ፳፯ 4 | ፳፰ 5 | ፳፱ 6<br>**ቀዳማዊ አጼ ቴዎድሮስ፡**<br>በሺ፬፻፬ ዓ.ም. የተቀባው ስመ-ጥሩው ጻድቅ ኢትዮጵያዊ | ፴ የላስታ ላል-7<br>ይበላል [ላሊበላ] አብያተ ክርስቲያን በ፲፭፻፳፭ ዓ.ም. በአሕመድ ግራኝ ጦር የተበዘበዙበት | ማስታወሻ፡- |

"ወነበበ መልአከ-እግዚአብሔር፡ ለፊልጶስ፤ ወይቤሎ፡- 'ተንሥእ! ወሑር፡ ጊዜ ቀትር፣ ፍኖተ በድው፡ ዘያወርድ፡ እምኢየሩሳሌም፡ ለጋዛ! ወተንሥአ፤ ወሖረ፤ ወረከበ፡ ብእሴ፡ እምሰብአ ኢትዮጵያ፣ ኀፅዋ ለሕንደኬ፡ ንግሥተ-ኢትዮጵያ፥ ወመጋቢሃ ውእቱ፡ ላዕለ ኵሉ መዛግብቲሃ። ወሖረ ኢየሩሳሌም ይስግድ። ወእንዘ ይገብእ፡ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ፤ ወያነብብ፡ መጽሓፈ ኢሳይያስ ነቢይ። ወይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ።- 'ሑር! ትልዎ፡ ለዝ ሠረገላ!' ...ወይቤሎ ኀፅው፥ ...ወአስተብቍዖ ለፊልጶስ፡ ከመ ይዕርግ፥ ወይንበር ኀቡረ ምስሌሁ። የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፊልጶስን፡ 'በቀትር ጊዜ ተነሥተህ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ወደጋዛ ወደሚያወርደው፡ የምድረ-በዳ መንገድ ኺድ!' አለው። ተነሥቶም ኼደ። እነሆም፡ ከኢትዮጵያ ሰዎች የኾነ አንድ ሰውን አገኘ። እርሱም፡ 'ሕንደኬ' የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ጃንደረባዋ የኾነ፥ በሀብቷም ላይ ኹሉ የሠለጠነ፡ በዥሮንደ ነው፤ ወደኢየሩሳሌም መጥቶ፡ ከተሳለመ በኋላ፡ በሠረገላው ተቀምጦ ሲመለስ፡ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሓፍ እያነበበ ነበረ። መንፈስ ቅዱስም፡ ፊልጶስን፡- 'ኺድ! ይህን ሠረገላ ተከተል!' አለው። ...ጃንደረባውም፡ ፊልጶስን አናገረው፤ ወደሠረገላው ወጥቶ፡ ከእርሱ ጋር ዐብሮት እንዲቀመጥም ለመነው።" የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ የኾነው ጃንደረባም፡ ወዲያው፡ "ኢየሱስ መሲሕ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ አምናለሁ!" ስላለ፡ ፊልጶስ፡ እዚያው አጠመቀው። ከጥምቀቱም በኋላ፡ ጃንደረባው አቤሜሌክ፡ በተደረገለት፡ መለኮታዊ የቸርነት ሥራ፥ በተቀዳጀውም፡ ዘለዓለማዊ፡ የመንፈስ ቅዱስ ብፅዕና፡ በደስታ እጅግ ተመሥጦ ስለነበረ፡ ፊልጶስ፡ ከአጠገቡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ የመወሰዱን ተአምር ሳያስተውል፡ ዝም ብሎ፡ የሠረገላ መንገዱን ቀጠለ። (የሐዋ. ፰፥ ፳፮-፵።)

| የሰኔ ወር ምንባብ፡- | የሓዋርያት ሥራ እና ንኡሳኑ መልእክታት። |
|---|---|
| | |

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ሓምሌ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Hamley (July-Aug., 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ፴ ማርያም ክብራ፡ 6<br>(እቴጌ ናያድ ሞገሳ)<br>የአጼ ናያድ ሚስት | ማስታወሻ፡- | | | | | ፩ 8 |
| ፪ 9<br>ታዴዎስ፡<br>ከ፲፪ቱ ሓዋርያት | ፫ 10 | ፬ 11<br>የጾመ ሓዋርያት<br>ማብቂያ | ፭ 12<br>በዓለ ቅዱሳን<br>ሓዋርያት፡<br>ጴጥሮስ ወጳውሎስ | ፮ 13<br>ዕርገተ<br>እዝራ | ፯ ሥሉስ ቅዱስ 14<br>በአብርሃም ቤት<br>የተገኙበት።<br>በ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በፋሺስት<br>ጣልያን ጦር በሰማዕትነት<br>የተሠዉት ፳፭ቱ የደብረ-ሊባኖስ<br>ገዳም አባላት | ፰ 15 |
| ፱ 16 | ፲ 17 | ፲፩ 18 | ፲፪ 19 | ፲፫ 20 | ፲፬ 21 | ፲፭ 22<br>ኤፍሬም፡<br>የውዳሴ<br>ማርያም<br>ደራሲ |
| ፲፮ 23 | ፲፯ 24<br>ነቢዩ ዮናስ፡<br>ነነዌ የገባበት | ፲፰ 25<br>ያዕቆብ፡ የጌታ ዘመድና<br>በኢየሩሳሌም፡የቤተ-<br>ክርስቲያን የመጀመሪያው<br>ሊቀ-ካህና ትና ሰማዕት።<br>የኢትዮጵያ ልጆች፡<br>ጦቢያና ጦቢት | ፲፱ 26<br>ቅዱስ ገብርኤል፡<br>ሊቀ-መላእክት፡ ሕፃኑን<br>ሰማዕት ቂርቆስንና<br>እናቱን ኢየሉጣን፡<br>ተጥለውበት ከሚነድ<br>ድባቸው እሳት ያዳነበት | ፳ 27 | ፳፩ 28<br>አጼ ሠርፀ-ድንግል፡<br>ሃይማኖታዊው ተጋዳይ | ፳፪ 29<br>ቅዱስ<br>ዑራኤል፡<br>ሊቀ-<br>መላእክት |
| ፳፫ 30<br>ቅዱስ ጴጥሮስ<br>ኢትዮጵያዊው ገዳማዊ<br>ሰማዕት፡ በ፲፱፻፳፰<br>ዓ. ም. በፋሺስት<br>ጣልያን ጦር የተገደለው | ፳፬ 31<br>የደብረ-ሊባኖስ ገዳም፡<br>በ፲፭፻፳፫ ዓ.ም. በአሕመድ<br>ግራኝ የተቃጠለበት፤<br>ከአባሎቹም መካከል፡<br>እየራሳቸውን፡ ለእሳቱ፡<br>በሰማዕትነት የማገዱበት | ፳፭ 1<br>ገዳማዊ ሕፃን-ሞአ<br>ኢትዮጵያዊ | ፳፮ ጻድቅ 2<br>ዮሴፍ ኢትዮጵያዊ፡<br>ሕፃኑን ኢየሱስንና<br>እናቱን ድንግል<br>ማርያምን ለማገልገል<br>በመብቃቱ፡ በፈጣሪ<br>የተመረጠ | ፳፯ 3 | ፳፰ 4 | ፳፱ 5 |

**"ወአንጕርጐሩ አይሁድ በእንቲአሁ፣ እስመ ይቤሎሙ፡- 'አነ ውእቱ፡ ኅብስተ-ሕይወት፣ ዘወረደ እምሰማይ!' ወይቤሉ፡- 'እፎ ይክል ዝንቱ፡ የሀበነ ሥጋሁ ንብላዕ?' እንግዴህ፡ ኢየሱስ፡ 'ከሰማይ የወረደ እንጀራ፡ እኔ ነኝ!' ስላላቸው፡ አይሁድ፡ ስለእርሱ አንጐራጐሩ፤ 'እንዴትስ፡ ይህ ሰው፡ ሥጋውን እንበላ ዘንድ ሊሰጠን ይችላል?' አሉም።" ከዚህ የተነሣ፡ "ወብዙኃን፡ እምአርዳኢሁ፡ እለ ሰምዑ፡ ወይቤሉ፡ 'ዕፁብ ዝንቱ ነገር! ወመኑ ይክል ሰሚያቶ? ...ወገብኡ ድኅሬሆሙ፤ ወኢሖሩ እንከ ምስሌሁ።' ከደቀ-መዛሙርቱ መካከል ሳይቀር፡ ይህን የሰሙ፡ ብዙዎች፡ 'ይህ፡ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው! ማን ሊሰማው ይችላል?' ብለው፡ እርሱን መከተልን ትተው፡ ወደኋላቸው ተመለሱ።" በዚህ ጊዜ፡ ጌታችን ኢየሱስ መሲሕ፡ "አማን አማን እብለክሙ! እመ ኢበላዕክሙ ሥጋሁ፡ ለወልደ ዕጓለ-እመሕያው፣ ወኢሰተይክሙ ደሞ፡ አልብክሙ ሕይወት ላዕሌክሙ። ዘበልዐ ሥጋየ፥ ወሰትየ ደምየ፡ ቦ ሕይወት ዘለዓለም። ወአነ አነሥኦ፡ በደኃሪት ዕለት። እውነት እውነት እላችኋለሁ! የማርያምን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ፡ በእየራሳችሁ፡ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን፡ የበላ፤ ደሜንም፡ የጠጣ፡ የዘለዓለም ሕይወት አለው። እኔም፡ በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" ሲል፡ ሊድን ለሚፈልግ፡ ለዓለሙ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ የመጨረሻ ዐዋጅ የኾነውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ገልጦና አስረግጦ ተናገረ።** (የሓ.፮፥ ፵፩-፶፱)

| የሓምሌ ወር ምንባብ፡- | ደቂቀ ነቢያት እና የዮሓንስ ምሥራች። |
|---|---|

# ፪ሺ፱ (፳፻፱) ዓመተ-ምሕረት ወርኀ ነሓሴ ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

2009 Era of Mercy. Month of Nehassey (Aug.-Sept., 2017). Year of Matthew the Evangelist

| እሑድ<br>Sunday | ሰኞ<br>Monday | ማግሰኞ<br>Tuesday | ረቡዕ<br>Wednesday | ሓሙስ<br>Thursday | ዓርብ<br>Friday | ሰንበት<br>Saturday |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ማስታወሻ፡- | ፩ የፍልሰታ 7<br>ለማርያም ጾምና ሱባዔ መግቢያ።<br>ጌታን የገነዙት ዮሴፍና ኒቆዲሞስ | ፪ 8 | ፫ 9 | ፬ 10 | ፭ 11<br>ገዳማዊ ፊልጶስ፡ ዘደብረ-ቢዘን | ፮ ማርያም12<br>መግደላዊት፡ የጌታን ትንሣኤ፡ ቀድማ አይታ፡ ያበሠረች |
| ፯ 13<br>አጼ ናዖድ<br>የመልክዓ ማርያምና የመልክዓ ኢየሱስ ደራሲ | ፰ 14 | ፱ 15 | ፲ 16 | ፲፩ 17 | ፲፪ 18 | ፲፫ ቡሔ19<br>ደብረ-ታቦር፡<br>ጌታ፡በግርማ መለኮቱ የታየበት |
| ፲፬ 20<br>የፍልሰታ ለማርያም ሱባዔ ማብቂያ | ፲፭ 21<br>የፍልሰታ ለማርያም ጾም ማብቂያ | ፲፮ 22<br>የድንግል ማርያም፡ በዓለ ፍልሰታ | ፲፯ 23 | ፲፰ 24<br>አዝማች አዳሉ፡<br>በአሕመድ ግራኝ ወረራ የተሠዋ ኢትዮጵያዊ ጀግና | ፲፱ 25 | ፳ 26 |
| ፳፩ 27 | ፳፪ 28 | ፳፫ ገዳማዊ 29<br>ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፡<br>ኢትዮጵያዊው የመዓዛ ቅዳሴና የሰዓታት፥ የሌሎችም ጸሎታት ደራሲ | ፳፬ በ፲፪ኛው ፻ ዓመት 30<br>ኢትዮጵያዊው ሥርዓተ መንግሥት፡ በሰላም ወደሰሎሞናዊው አገዛዝ እንዲመለስ ያስማማ፡ እጨጌ ተክለ-ሃይማኖት።<br>ክርስቶስ ሠምራ፡<br>ለኢትዮጵያዊነት አብነት | ፳፭ 31 | ፳፮ 1 | ፳፯ 2<br>አጼ ዓምደ ጽዮን፡<br>ስለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የተጋደለ |
| ፳፰ 3<br>አብርሃም፥ ይስሓቅና ያዕቆብ | ፳፱ 4<br>ንዋየ-ክርስቶስ (አለቃ ዘካርያስ)፡ እስላም ሣለ እስላሞችን፡ በቁርዓና ቸው የረታና ብዙዎቹ ን፡ ያስጠመቀ ኢትዮጵያዊ ሓዋርያ፡ ለኢትዮጵያዊነት፡ አብነትና ድልድይ የኾነ | ፴ ኢትዮጵያዊው 5<br>መልከ-ጼዴቅ፡ እርሱም ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኖኅ የተረከበው የፊተኛው፤ አብርሃምን በባረከው፡ በማእከላዊው አማካይነት፡ ለመጨረሻውና ለአማናዊው መልከ ጼዴቅ፡ ኢየሱስ መሲሕ ቀዳሚ አርአያ የኾነው | ጳ ጉ ሜ | | | |
| ጳ ጉ ሜ<br>፭ 10<br>ዓሞጽ ነቢይ።<br>የንስሓ ጾም ማብቂያ | | | ፩ 6<br>የንስሓ ጾም መግቢያ | ፪ 7 | ፫ ቅዱስ 8<br>ሩፋኤል፡ ሊቀ-መላእክት።<br>አጼ ዘርዓ ያዕቆብ | ፬ 9<br>የቅዱሳንና የቅዱሳት ኹሉ መታሰቢያ። |

መልአኩ፡ ቅዱስ ገብርኤል፡ ድንግል ማርያምን፡ "ተፈሥሒ ፍሥሕት፡አ ምልዕተ-ጸጋ፡ እግዚአብሔር ምስሌኪ! ቡርክት አንቲ እምአንስት! ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽው፥ እግዚአብሔርም፡ ካንቺ ጋራ የኾነው፡ አንቺ፡ ጸጋን የተመላሽ፡ ደስተኛቱ ሆይ! ደስ ይበልሽ!" አላት። መንፈስ ቅዱስ የመላባት ኤልሣቤጥም፡ "ቡርክት አንቲ እምአንስት! ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ! ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ አንቺ የተባረክሽ ነሽ! የማሕፀንሽም ፍሬ፡ የተባረከ ነው!" አለቻት። ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያምም፡ "ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትሐሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ ለአመቱ! ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ! እስመ ገብረ ሊተ፤ ኃይለ ዐቢያተ! ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን፡ ታልቀዋለች! መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል! የአገልጋዩን መከራ አይቷልና! እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልድ ኹሉ፡ ያመሰግኑኛል! እርሱ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ተአምራትን አድርጓልና። (ሉቃ. ፩፥ ፳፮-፶።)

| | |
|---|---|
| የነሓሴ እና የጳጉሜ ወራት ምንባባት፡- | መጽሓፈ ጦቢት እና የሉቃስ ምሥራች። |